## ለእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፥
## ለንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ
## የተጻፉ እለቄጥሩ ጦማሮችና ከእርሳቸው የተሰጡ መልሶች።

---

### ከወ/ሮ ፍቅርተ የተላከ፡ የመጀመሪያ እ-ጦማር።

በቅድሚያ፡ በአገልግሎትዎ የኀዋ ሰሌዳ ላይ ያሠፈሩዋቸው የጾመ ኢትዮጵያ መልእክትና የምሕላ ጸሎቶች፥ እንዲሁም፡ ከዚያም በፊት፡ በተከታታይ የቀረቡት መልእክቶች ኹሉ፡ በጣም ጠቃሚ ኾነው አግኝቻቸዋለሁና፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብያለሁ!

በመቀጠል፡ የተወሰኑ ጥያቄዎች ስላሉኝ፡ ለማቅረብ ይፈቀድልኝ፡-

፩. ለሕፃናት ማስተማርያ የሚኾን ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ፡ በክፍለ ትምህርቶቹ ዕቅድ ውስጥ፡ ስለካህኑ መልከ ጼዴቅና ስለሰብአ ሰገል ታሪክ ለማስገባት ስፈልግ፡ በቤተ ክርስቲያን የሚነገረው ታሪክና ከእርስዎ መጽሓፍ የማነብበው ታሪክ፡ አልታረቅልሽ አሉኝ። ለምሳሌ፡ "መልከ ጼዴቅ፡ በድንግልና የኖረ ነው!" ብሎ፡ የቤተ ክርስቲያኑ አንድምታ ይገልጻል። በእርስዎ መጽሓፍ ደግሞ፡ ሚስቱ፡ እንተላ ትባል እንደነበረ ይገልጻል። "መጽሓፈ አብርሂት" በተባለው፡ በቅርቡ፡ በመሪ ራስ አማን በላይ፡ ከጥንት ብራና መጻሕፍት የተተረጎመው መጽሓፍ ደግሞ፡ መልከ ጼዴቅን፡ "ጌራራ" የተባለው መኾኑን ከገለጸ በኋላ፡ ሚስቱ፡ "ሳሌም" እንደምትባልና ኢትዮጲስ ደግሞ፡ የእነርሱ ልጅ እንደኾነ፥ ከዚያም፡ እርሱ፡ ራሱ፡ በመልከ ጼዴቅነት ተሹሞ፡ ወደኢትዮጵያ በመግባት፡ ኢትዮጵያን እንደመሠረተ፡ እንዲሁም፡ ልጆችን እንደወለደ ይገልጻል።

እና በጥልቀት፡ ታሪኮቹ ውስጥ መግባት፡ በሕፃናት ደረጃ፡ አስፈላጊ ባይኾንም፡ ቢያንስ፡ "'መልከ ጼዴቅ' የምንለው፡ የእኛ አባት ኢትዮጲስ፡ የት ነው የኖረው?" የሚለውን፡ በትክክል ማስፈር፡ የሚጠይቅ ኾኖ አገኘሁት። ደግሞም፡ በቀጣይ፡ "የክፍል ደረጃዎች፡ የበለጠ፡ በስፋት፡ ሊያውቁት ይገባል!" ብዬ አምናለሁ። እናም፡ በእኔ ግምት፡ በእርስዎ መጽሓፍ ላይ የተጻፈው፡ "የመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ"፡ "ጌራራ" የተባለው፡ የኢየሩሳሌሙ መልከ ጼዴቅ ሲኾን፡ "መካከለኛው መልከ ጼዴቅ" ያሉት፡ ምናልባት፡ ኢትዮጲስ ሊኾን ይችላል ብዬ ገመትሁ። ነገር ግን፡ ያ አያስኬድም፤ ምክንያቱም፡ የመጀመሪያው፡ የሦስቱ ዘር ውሕደት፡ ራሱ፡ "ኢትዮጲስ" የተባለው፡ መልከ ጼዴቅ ስለኾነ ነው።

እናም፡ ይህችን፡ ያስታርቁልኝ ዘንድ፡ በአክብሮት እጠይቃለሁ። የርስዎ መጽሐፍ ላይ ያለውን ታሪክ፡ ሙሉ ለሙሉ አስገብቼ፡ በዋቢ መጻሕፍት፡ የርስዎን መጽሐፍ ላስገባበት ፈልጌ ነበር። ነገር ግን፡ ከተለመደው ታሪክ፡ ወጣ ያለ ነገር ሲተረክ፡ በብዙኃኑ ላይ የሚፈጠረውን ስሜት በሚገባ ያውቁታል።

በአንድ ጎዋ ሰሌዳ ላይ ተጽፎ እንዳነበብኩት፡ ስለዚህ ታሪክ፡ "'መጽሐፈ አክሱም ጥንት' የሚባል መጽሐፍ ላይ፡ በሰፊው የተብራራ ነገር ሳይኖር አይቀርም!" የሚል አየሁ። እርስዎ፡ ስለመልከ ጼዴቅ፡ ያቀረቡበት መንገድ፡ ከዚያ መጽሐፍ ጋር፡ ተመሳሳይነት ይኖረው ይኾን?

፪. ሌላው ደግሞ፡ የሰብአ ሰገል ጉዳይ ነው። እርስዎ እንደጻፉት፡ ሦስቱም፡ ኢትዮጵያውያን አይደሉም። ይልቁንም፡ ሴማዊ፥ ካማዊና ያፌታዊ ናቸው። የተለመደው አባባል ግን፡ "አንዱ፡ ኢትዮጵያዊ ነው" የሚል ነው። እሱም፡ "አጼ ባዜን ነው" የሚል ነው። ይህንን ትምህርት፡ እርስዎም፡ በመጽሐፍዎ ላይ ጠቅሰውታል። ስሕተት መኾኑንም ጭምር ጽፈዋል። የተለመደው ታሪክ፡ "የሳባና የዐረብ፥ የተርሴስና የፋርስ ነገሥታት፡ እጅ መንሻን ያመጡለታል!" የሚለውን የዳዊትን ትንቢት ተከትሎ የሚባል ነው። ይህ፡ ምናልባት፡ እርሶ ከጻፉት ጋር አይጋጭም ይኾናል። ነገር ግን፡ አኹንም፡ "አጼ ባዜንና ሌሎች የክልል መሳፍንት (የወሎ፥ የእናርያ፥ ወዘተ ንጉሦች)፡ ወደቤተ ልሔም ኼደው፡ እጅ መንሻን አግብተዋል!" የሚለው ታሪክ፡ የበለጠ ተቀባይነት ኖሮት፡ በየመጻሕፍቱ ላይ ተጽፏል። መጽሐፈ አብርሂትም ላይ እንዲሁ፡ "ጥንታዊ መጻሕፍት ዘግበውታል!" የሚል ታሪክ አለ።

እና፡ ይሄም እንደዚያው አልታረቀልኝም። የእርስዎ ምንጭ፡ ከየት ነው? ከነዚህስ ጽሑፎች ጋር በርግጥ የሚጋጭ ነው? ወይስ፡ እኔ ማስታረቅ ስላልቻልኩ ይኾን?

፫. የሚቀጥለው ጥያቄዬ፡ የእኔ፡ የግል ጥያቄ ነው። በኹለቱ ሲኖዶሶች መሃል የደረሰውን መወጋገዝ ተከትሎ፡ በጎዋ ሰሌዳዎ ላይ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡ ክህነታዊ አገልግሎቷ ቆሟል!" በማለት፡ ያወጡት መልእክት፡ ኹሌም ይረብሸኛል። ክህነታዊ አገልግሎቷ ከተቋረጠ ደግሞ፡ ቅዱስ ቁርባኑም፡ የውሸት ሊኾንብን እኮ ነው? እኔ እየኼድኩ ያለሁበት የሰበካ ቤተ ክርስቲያን፡ በአሜሪካ፡ የአንዱ ክፍል መዲና በኾነችው ከተማ የሚገኝ ኾኖ፡ "ኪዳነ ምሕረት" ይባላል። "ገለልተኛ" ተብሎ፡ የኹለቱም ጳጳሳት ስም አይጠራበትም። የሚተዳደረውም፡ በቦርድ ነው። ባለፈው የገና ጾም ወቅት፡ እኔና ባለቤቴ ኼደን፡ ቅዱስ ቁርባን ተቀብለናል። ነገር ግን፡ ኹሌም፡ ይህ መልእክት ይረብሸኛል። ቁርባኑ፡ በርግጥ፡ ቁርባን አይደለምን? "አዎን! ቁርባን አይደለም!" ብለ፡ ይህን ኹሉ ሕዝበ ክርስቲያንና በየቤተ ክርስቲያኑ የሚደረገውን የጸሎት ልፋት፡ ከንቱ ያደረግሁ ይመስለኛል።

“ቁርባን ነው!” ብል፡ ውግዘት ቀላል አይደለምና፡ ቀድሞ፡ በሌሎች አባቶች፥ አኹን ደግሞ፡ እርስ በርሳቸው ከተወጋገዙ፣ በርግጥም ተወጋግዘዋልና፡ እውነትም፡ የክህነት አገልግሎቱ ቆሟል። ግን፡ የተራው ካህን ክህነትም፡ በዚህ ምክንያት ይሻራልን? ኅብስቱንና ወይኑን፡ ወደሥጋና ደም እንዲለወጡ ማድረግ አይችልምን? ካልቻለስ፡ የት ኼደን እንቁረብ? ቁርባን ቆሟልን? ለዚህ፡ መፍትሔ ሳይገኝለት፡ ስለክርስትና መዘባረቅ፡ ከንቱ እየመሰለኝ፡ ተቸግሬያለሁና ይርዱኝ። ምላሽዎን፡ በጉጉት እጠባበቃለሁ።

በስተመጨረሻ፡ ታናሽ እኅቴ፡ ለትምህርት፡ ወደጎንደር ስትኼድ፡ ያለፈው መስከረም ወር የገጠማትን ላጫውትዎት! መጻሕፍትዎን አስገዝቼ፡ ወደሓረር ካስመጣሁ በኋላ፡ እንዲያነብቡት፡ ለታናሽ እኅቴና ለወንድሞቼ ሰጠኋቸው። እናም፡ ይህችው እኅቴ፡ መጽሓፉን ይዛ፡ ወደጎንደር፡ ለትምህርቷ ስትኼድ፡ ከሓረር፡ በሕዝብ ማጓጓዣ ተሣፍራ፡ ጒዞ ጀመረች። “ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!” የሚለውን መጽሓፍዎን፡ በማጓጓዣው ውስጥ እንዳለች፡ ማንበብ ጀመረች። በኋላም፡ “ሂርና” እተባለው ቦታ ሲደርሱ፡ የምትጓዝበት ተሽከርካሪ፡ ልጓሙን በጠሰ። ልጓሙን በጥሶ ሲምዘገዘግና ሰዉ ሲጯጯህ፡ እርሷ፡ መጽሓፉ ላይ ተተክላ፡ አቀርቅራ ስለነበረ፡ ለአደጋው፡ ምንም ትኩረት አልሰጠችም።ከወንበሩዋም አልተነሣችም። መኪናው፡ እየተምዘገዘገ ኼዶ፡ ከመንገዱ ጠርዝ ካለ፡ ግንብ ጋር ተላተመ። ሲጯጯሁ የነበሩት፡ በብዛት ተጎዱ። በተለይ፡ ተሽከርካሪው የተጋጨው፡ በርሷ በኩል ስለነበረ፡ በርሷ መደዳ ከተቀመጡት መሃል፡ ጒዳት ያልደረሰባቸው አልነበሩም። እርሷ ብቻ ምንም ሳትኾን፡ በመስኮት ሾልካ ወጣችና፡ በአነስተኛ፡ የሕዝብ ማጓጓዣ ተሣፍራ፡ ወደሓረር ተመለሰች። ቤት ስትደርስም፡ ከድንጋጤና ከመስታወት ርጋፊ በቀር፡ ምንም አልነበረባትም።

“አንቺ፡ ምን እየሠራሽ ነበር?” ስላት፡ “‘ሰውየው፡ እንዴት፡ እንዴት ነው የሚጽፉት?’ እያልኩ ስገረም ነበር!” አለችኝ። ስለእውነተኛዋ ኢትዮጵያ እና ስለሓሰተኛዋ ኢትዮጵያ ንጽጽር እያነበበች ነበር። መጽሓፉም፡ የሰው ደምና የመስታወት ጭረት፡ ሽፋኑን አበላሽቶት ደረሰ። “ተአምር ነው!” ብዬ አለፍኩት። በመጽሓፉ የተጻፈው፡ ምን ይኹን ምን፡ ባያነብም፡ መላው ቤተሰብ፡ መጽሓፉን አመስግኗል። በተለይ አባቴ፡ “እንኳን እግዚአብሔር፡ ልጅህን አተረፈልህ!” ሊል የመጣውን ኹሉ፡ መጽሓፉን፡ “ለማስረጃነት ተርእዮ” አስቀምጦ፡ ሲያስጎበኝ ዋለ። ነገር፡ አልያያዝ ብሎት፡ አልተሳካለትም እንጂ፡ የመጽሓፉን ይዘት፡ እኔ ጨምቄ እንዳስረዳሁት አድርጎ፡ ለሰዎች ሊተርክ ኹሉ ከጅሎት ነበር። አልገባ ብሏቸው፡ ዝም አሉት እንጂ። ኹኔታውን ሳስታውስ፡ አኹን እስቃለሁ። እኅቴ፡ በቀጣይ ጒዞዋ፡ በአየር መጓጓዣ ነው የኼደችው። መጽሓፉንም ይዛ ኼደች። “ደግሞ፡ በራሪው ቢከሰከስስ?!” ብላ ሳይኾን አይቀርም።

## ለዚህ፡ የመጀመሪያ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

ለወ/ሮ ፍቅርተ፡-

በእ-ጦማር አማካይነት የጻፉልን፡ ቍምነገር የመላበት ደብዳቤዎ፡ በጊዜው ደርሶኛል፤ በውስጡ፡ ጾመ ኢትዮጵያንና በጎዋ ሰሌዳችን ላይ የሚወጡትን መልእክቶች በሚመለከት፡ ስለገለጹልን መልካም ምኞትና ስለሠነዘርዋቸው በጎ አስተያየቶች ጭምር፡ እግዜር ይስጥልን!

በቅርቡ፡ በወላጆችዎና በቀረው ቤተሰብዎ መካከል ለመገኘት ላበቁዎ ቸር ፈጣሪና ለቅድስት እናቱ፡ እንደመባዕ የሚቆጠሩልዎትን መጻሕፍታችንን በግዢ ወስደውላቸው፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" የሚያሰኘንን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን መልእክት: ከቃልዎና ከመጻሕፍቱ እንዲያገኙ ማድረግዎ፡ ፈጣሪዎና ቅድስት እናቱ የሚያውቁትን፡ እውነተኛ ማንነትዎን፡ እኛም፡ እንደገና አረጋግጠን እንድናውቀው አድርገዋል። ቤተሰቦችዎን፡ ለእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ሕይወት ለማብቃት፡ በሩቅም ኾነ በቅርብ ኾነው፡ የሚያደርጉትን ጥረት ከማድነቃችን ጋር፡ በአኹኑ ጕብኝትዎ ጊዜ፡ በተለይ በአባትዎ አንደበት ተነግሮ ስለነበረው ቃልና በመንገደኛዋ እኅትዎ ላይ ደርሶ፡ በተአምር ስለተረፈችበት አደጋ ያሰሙን ዜና፡ ልባዊ የእርካታን መንፈስ ያሳደረብን ከመኾኑ ጋር፡ በተለይ እኅትዎን፡ ከአካል ጕዳት ሳይቀር ላዳነው አምላካችን፡ ልባዊ ምስጋናችንን አቅርበናል።

ከዚህ በመቀጠል፡ ለጥያቄዎችዎ፡ አግባብነት ያላቸውን መልሶች፡ እንደሚከተለው፡ በየመልኩ አሥፍረናቸዋል።

፩ኛ፡- መልከ ጼዴቅ፡ የማዕርግ ስም እንደመኾኑ፡ ከኖኅ በኋላ፡ በዚህ ማዕርግ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ ከተቀመጡት አጼዎች መካከል፡ ዝክረ ነገራቸው፡ በቅዱሳንና በቅዱሳት ልቦና ተመዝግቦ፡ በይበልጥ የሚነበበውና በእነዚሁ አንደበት የሚነገረው፥ እንዲሁም፡ በየዘመናቸው፡ እንግዳ የኾኑ፡ የእግዚአብሔር ድንቃድንቅ ድርጊቶች ስለተፈጸሙ፡ ስማቸው፡ በገናንነት የሚጠራው፡ ሦስቱ ናቸው፤ እነዚህም፡ "ኢትዮጲስ" የተባለውና ሚስቱ፡ "እንተላ" የተባለችው፥ ከኖኅ፡ የቅዱሱን ኪዳን ሕያው ቅርስ፡ በውርስ የተረከበውና ኢየሩሳሌምን የቈረቈረው፡ <u>የመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ</u> ነው።

የመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ፡ ይኸው ኢትዮጲስና ይህችው ሚስቱ፡ እንተላ፡ የመጨረሻውንና ዘለዓለማዊዉን፥ አማናዊዉንም መልከ ጼዴቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በወለዱት፡ በመለኮታዊው አባቱ፡ በእግዚአብሔር አብና በሰብአዊት እናቱ፡ በድንግል ማርያም ተመስለዋል። አብርሃምን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቃው፥ በድንግልናዊነቱና በብሕትውናውም፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌው የኾነለት፡ ሌላው፡ የዘር ሓረግ ተከታዩ መልከ ጼዴቅ፡ መካከለኛው ነው።

ፈጣሪ፡ ለቅዱሱ ኪዳን መነሻ ይኾን ዘንድ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን የወጠነውን፥ በመካከለኛውም ዘመን፡ ጠብቆ ያኖረውንና በመጨረሻው የተስፋው ፍሬያማ ቀን፡ በተግባር የፈጸመውን ሥርዓተ ኃብቻ፡ ለዘለዓለማዊው ሕያውነት ሊያበቃው፡ ከመሠረቱ ዐቅዶ ያዘጋጀበትን መለኮታዊ ምሥጢሩን፡ በመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ፡ በኢትዮጲስና በእንተላ ኃብቻና ትዳር፡ ቀዳሚ ምሳሌነትና አርአያነት፡ እንዴት አድርጎ እንደከሠተው፡ በማስተዋል መመልከቱ፡ ለማንኛውም እውነተኛ ምእመን፡ ከቶ አያዳግተውም። ይኸውም፡ በመለኮታዊ ህልውናው እየኖረ ያለው እግዚአብሔር አብ፡ ጥንት፡ ከፍጥረት በፊት፡ አስቀድሞ የወለደውንና በዚያው የአንድነት መለኮታዊ ህልውና የሚኖረውን፡ "እግዚአብሔር ወልድ" የተባለውን ልጁን፡ በፍጻሜ ዘመን፡ እንደገና አባት ኾኖ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" በተባለ ልዩ ስም፡ ራሷን፡ በገዛ ፍላጎቷና ምርጫዋ፡ ለእግዚአብሔር እናትነት ካበቃችው፡ ከሴቷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚያው፡ በአንድነት መለኮታዊ ህልውና በሚኖረው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በሰውነት መውለዱ፡ ይህን መለኮታዊ እውነታ አረጋግጦ የሚመሰክር ስለኾነ ነው። ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ የሓዋርያው ቃል ያጸናዋል፦

***"ወይእዜኒ፡ ክርስቶስ፡ ቀደመ፡ ተንሥአ፡ እምኵሎሙ ሰብእ ምውታን። ...አሜሃ ይከውን ማኅለቅትሰ፡ አመ ተወፈየ እግዚአብሔር አብ፡ መንግሥቶ፥ ወአመ ተስዕረ ኵሉ መኰንን፥ ወኵሉ ንጉሥ፥ ወኵሉ ኃይል። እስመ ሀለዎ ይንግሥ፡ እስከአመ ይገብኡ፡ ኵሉ ጸላእቱ፡ ታሕተ እገሪሁ። ወእምዝ ይሰዐር፡ ደኃሪ ጸላኢ፡ ዘውእቱ ሞት፤ እንዘኒ ያገርር ኵሎ፡ ታሕተ እገሪሁ። ወአመ ይቤ፡ 'ኵሉ ይገርር ሎቱ!' ወባሕቱ ይትዐወቅ ከመ ይንእስ፡ እምዘአግረረ ሎቱ ኵሎ። ወአመ ኵሉ ገነየ ሎቱ፡ ይእተ ዕለተ፡ ወልድኒ ይገኒ፡ ለዘአግነየ ሎቱ ኵሎ [ለእግዚአብሔር አብ]፡ ከመ ይኩን እግዚአ በኵሉ፥ ወላዕለ ኵሉ።"***

ማለትም፡ "አኹን ግን፡ ክርስቶስ፡ ላንቀላፉት፡ በኵራት ኾኖ፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል። ...በኋላም፡ እግዚአብሔር አብ፡ መንግሥቱን፡ በተረከበ ጊዜ፥ አለቅነትንም ኹሉና ሥልጣንን ኹሉ፥ ኃይልንም፡ በሻረ ጊዜ፡ ፍጻሜ ይኾናል። ጠላቶቹን ኹሉ፡ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ፡ ሊነግሥ ይገባዋልና። የኋለኛው ጠላት፥ የሚሻረው፡ ሞት ነው፤ ኹሉን፡ ከእግሩ በታች አስገዝቷልና። ነገር ግን፡ 'ኹሉ ተገዝቷል!' ሲል፡ ኹሉን ካስገዛለት በቀር መኾኑ፡ ግልጥ ነው። ኹሉ ከተገዛለት በኋላ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ኹሉ፡ በኹሉ ይኾን ዘንድ፡ በዚያን ጊዜ፡ ልጁ ራሱ ደግሞ፡ ኹሉን ላስገዛለት [ለእግዚአብሔር አብ] ይገዛል።" (፩ቆሮ. ፲፭፥ ፳-፳፰።)

በዚህ መሠረት፡ እርስዎ የጠቀስዋቸው፡ "ጌራራ" የተባለው፡ አንዱ፡ የኋለኛው መልከ ጼዴቅና ሚስቱ "ሳሌም" የወለዱት፡ ልጃቸው ዳግማዊ "ኢትዮጲስ" ተብሎ፡ ወደኢትዮጵያ እንደተመለሰ የሚነገረው ዜና መዋዕል፥ እንዲሁም፡ "መጽሓፈ አክሱም ጥንት" በሚባለው የታሪክ መጽሓፍ፥ በሌሎቹም፡ ተመሳሳይ መጻሕፍት ውስጥ፡ ስለመልከ ጼዴቆች የተመዘገበው ዝክረ ነገር፡ ከላይ ከተገለጸው ሓተታ ጋር እንደሚስማማ ግልጽ ነው።

፪ኛ፡- ሰብአ ሰገልን በሚመለከት የማቀርብልዎ ምላሽ፡ በመጻሕፍቴና በኀዋ ሰሌዳችን ውስጥ የተሰጠውን ሓተታ መሠረት ያደረገ ነው፤ ይኸውም፡ እንደእኛ እንደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ሕያው ትውፊት፡ "ኹሉም ኾኗል!" ወይም፡ "ኹለቱም ድርጊቶች ተፈጽመዋል! ስለዚህ፡ የሚስማማና የሚታረቅ አንድነት እንጂ፡ የሚቃረንና የሚጋጭ ልዩነት የለም!" የሚያሰኘው መደምደሚያ አሳብ ነው። ይህንም እውነታ፡ ከዚህ በሚከተለው አጭር ቃል ማስረዳት ይቻላል።

ማንነታቸው፡ በተለያየ መልክ የሚነገረው፡ ሦስቱ የኢትዮጵያ ነገሥታት፡ ሦስቱን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች የኾኑትን፡ የኢትዮጵያን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና በመወከል፡ በቤተ ልሔም መገኘታቸው እሙን ነው። በዚያ የተገኙትም፡ የዚችው፡ የእግዚአብሔር የኾነችው የኢትዮጵያ መንግሥት የዘውድ መሪዎች ለኾኑት እመቤትና ጌታ፡ ኹለቱን ታላላቅ ዓላማዎች ለመፈጸም ሲኾን፡ የመጀመሪያው ዓላማ፡ ለኢትዮጵያዊት ሃይማኖታቸውና አገራቸው፥ እናታቸውና ንግሥታቸው ድንግል ማርያም፥ የዐራስ ጥሪና "ዕንቍ ለጣትሽ! (ዕንቍጣጣሽ!)" ብለው፡ የደስታ ስጦታቸውን፡ በተቀደሰ ፍቅር ለማበርከት ነው።

ሌላው ተመሳሳዩ ዓላማ ደግሞ፡ እንደትንቢቱና እንደተስፋው ቃል፡ ፍጹም ሰው ኾኖ፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ሹመትና ሥልጣን፡ ከእርሷ ለተወለደው፥ ለዘለዓለማዊውና አማናዊው ኢትዮጵያዊ ካህናቸውና ሊቀ ካህናታቸው፥ ንጉሣቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ የአምልኮና የምስጋና መባአቸውን ከማቅረብ ጋር፡ የቅዱሱ ኪዳን ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ነው።

ከእኒህ ከኢትዮጵያኑ ውጭ፡ በቤተ ልሔም በረት ተገኝተው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ለተወለደውና "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ ለተጠራው፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ የወርቅ፥ የዕጣንና የከርቤ ግብርን ያቀረቡት ሦስቱ ነገሥታት፡ የመላው ዓለም ሕዝቦች፡ የዘር ግንዶች የኾኑትን፡ ሦስቱን፡ የሴም፥ የካምና የያፌት ነገዶችን የወከሉ ናቸው። ከእነዚህ፡ ከሦስቱ ነገሥታት መካከል አንዱ፡ "ኢትዮጵያዊ ነበር!" የሚለው ይትበሃል፡ ትክክል አይደለም።

ይህን ባዕድ የኾነ፡ የተሳሳተ ይትበሃል መቀበል፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን ማናጋት፥ ዓለም በተቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተመዘገቡትን ቃላትም ማስተሓቀር ስለሚኾን፡ በእጅጉ ልንጠነቀቅበት ያስፈልገናል። የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ፀሮች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕያዋን ውርሶቻችንና ቅርሶቻችን ላይ፡ በጽናት ከሚያኪያኺዷቸው፡ ከሌሎቹ ሥር ነቀል ዘመቻዎቻቸው መካከል፡ ይህ፡ አንዱ የሠመረላቸው መስሎ የሚታያቸው ሙከራቸውና ጥረታቸው መኾኑ፡ መዘንጋት የለበትም።

፫ኛ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከትና ስለሲኖዶሷ ከኹለት መከፈል፡ በመጻሕፍቴ ውስጥና በኅዋ ሰሌዳችን ላይ የሠፈሩትን ሓተታዎች፡ እርስዎም ስለተከታተልዋቸው፡ በሚበቃ የተረዱ ይመስለኛል። ከዚህ በኋላ ያለው ቀሪ ተግባር፡ የእያንዳንዱ ካህን፤ ወይም ምእመን፡ የግል ምርጫና ውሳኔ ነው፤ ምርጫውንና ውሳኔውን በምግባር ለመፈጸም ደግሞ፡ ከየራስ ኅሊና፥ ነጻነትና ሥልጣን ጋር፡ የመንፈስ ኃይሉንና ጽናቱን፡ እያንዳንዱ ካህን፥ ወይም ምእመን፡ ከፈጣሪ፡ በተፈጥሮና በሃይማኖት የተቀዳጀ ስለኾነ፡ ኹሉን ማድረግ ይቻለዋል። ዋናው ቍም ነገር፡ ፈጣሪያችን የሚፈልገውና የሚወድደው፥ የሚቀበለውም፡ "በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ" የሚቀርብለትን አምልኮ ብቻ መኾኑን፡ ለመላው ፍጥረተ ዓለም፡ እንዲህ ሲል፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ አስታውቋል፡-

"ወባሕቱ ትመጽእ ሰዓት፤ ወይእዜ ይእቲ፥ አመ እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን፡ ይሰግዱ ለአብ፡ በመንፈስ፥ ወበጽድቅ፤ እስመ አብኒ ዘከመዝ የኀሥሥ፡ እለ ይሰግዱ ሎቱ። እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ፣ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።"

ማለትም፡ "ነገር ግን፡ በእውነተኛ አምልኮ፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፡ በመንፈስና በእውነት አምልኮ፡ ለእግዚአብሔር አብ የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አኹንም ኾኗል። እግዚአብሔር አብ፡ እርሱን የሚያመልኩት፡ ይሰግዱለት ዘንድ፡ እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት፥ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሐ. ፬፥ ፳፫-፳፬።)

እኛም፡ እውነታው ይህ መኾኑን ካወቅን፡ የዛሬዋ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ በኅብረት፡ እንዲህ በይፋ በሚያካኺዱትና ጠንቁ፡ እነሆ፡ እስከእርስበርስ ደም መፋሰስና ዕልቂት በደረሰው፥ በዚህ የክህደትና የዓመፅ፥ የምንዝርናም ኃጢአት፡ ይኸው ቅዱሱ ኪዳን ፈርሶ፡ የሚቀርበው አምልኮና መሥዋዕት፡ እንዴት "እውነተኛና የመንፈስ ቅዱስ ይኾናል!" ብለን ልናስበው ይቻለናል? ፈጽሞ አይቻለንም። በውስጡ፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነት ያለችበት የአምልኮ ሰውነት፡ በዚህ ታላቅ ኃጢአት ምክንያት፡ በመለኮታዊው ውግዘት ታሥረው የሚገኙት፡ እኒህ ወገኖች የፈጸሙትን፡ ይህን የመሰለውን አሳዛኝ ኹኔታ ሊቀበለውና ሊስማማበት፥ ሊተባበርበትም ከቶ አይቻለውም። በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን ነገር በሚመለከት፡ እርስዎም፡ በውስጥዎ የተፈጠረብዎ ሁከትና እየተሰማዎ ያለው ችግር የተነሣሣብዎ፡ ኹለንተናዎ፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነትና አምልኮ ያደረበት ከመኾኑ የተነሣ ለመኾኑ፡ በቂ ምልክት ነው።

እንዲህ ባለ፡ የሃይማኖትና የምግባር አጣብቂኝ መካከል ለሚገኝ፡ ለማነኛውም ካህን፥ ወይም ምእመን፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "እግዚኦ! ውኁዳንኑ እንጋ እሙንቱ፡ እለ ይድኀኑ?" ማለትም፡ "ጌታ ሆይ! የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን?" ብሎ ለጠየቀው አንድ ሰው፡ እንዲህ ሲል የሰጠው መልስ፡ በቂ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ይኾነዋል፦ "<u>ተኀየሉ</u> ትባኡ፡ እንተ ጸባብ አንቀጽ! እብለክሙ፡ <u>ብዙኃን፡ እለ የኀሥሡ ይባኡ፤ ወኢይክሉ።</u> ...ወይመጽኡ እምጽባሕ፥ ወእምዕራብ፥ ወእምሰሜን፥ወእምደቡብ፤ ወይትፌሥሑ፡ በመንግሥተ እግዚአብሔር። ወይከውኑ፡ ደኃርት፡ ቀደምተ፤ ወቀደምት፡ ይከውኑ ደኃርተ።"

ማለትም፡ “በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ! እላችኋለሁና፤ ብዙዎች፡ ሊገቡ ይፈልጋሉ፤ አይችሉምም። …ከምሥራቅና ከምዕራብ፥ ከሰሜንና ከደቡብም ይመጣሉ፤ በእግዚአብሔርም መንግሥት፡ በማዕድ ይቀመጣሉ። እነሆም፡ ኋለኞች፡ ፊተኞች ይኾናሉ፤ ፊተኞችም፡ ኋለኞች ይኾናሉ።”

ደግሞም፡ “ባኡ እንተ ጸባብ አንቀጽ! እስመ ረኃብ አንቀጽ፥ ወስፍሕት ፍኖት፡ እንተ ትወስድ ውስተ ኃጕል፤ ወብዙኃን እሙንቱ እለ ይበውኡ ውስቴታ። ጥቀ ጸባብ አንቀጽ፥ ወጽዕቅት ፍኖት፡ እንተ ትወስድ ውስተ ሕይወት፤ ወውኁዳን እሙንቱ፡ እለ ይበውእዋ።”

ማለትም፡ “በጠበበው ደጅ ግቡ! ወደጥፋት የሚወስደው፡ ደጁ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፤ ወደርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው። ወደሕይወት የሚወስደው፡ ደጁ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፤ የሚያገኙትም፡ ጥቂቶች ናቸው።”

እዚህ ላይ፡ ለዚሁ ምእመን ሳይጠቀስለት የማይታለፍ፡ ሌላ፡ የጌታችን ታላቅና ቋሚ መመሪያና ማስጠንቀቂያ አለ፤ ይኸውም፡ ከዚያ ውስጥ፡ እጅግ በጥቂቱ የምጠቅስልዎ፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

“ወለዘኒ ኀፈረኒ፥ ወኀፈረ ቃልየ፡ የኀፍሮ ሎቱኒ ወልደ እጓለ እመሕያው፡ አመ ይመጽእ በስብሓቲሁ፥ ወበስብሓተ አቡሁ፣ ወዘቅዱሳን መላእክቲሁ። …ኵሉ፡ ዘየአምን ብየ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ ወዘሰ ክሕደኒ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። ኢይምሰልክሙ፡ ዘአምጻእኩ ሰላመ ለምድር! አላ፡ መጥባሕተ። ወመጻእኩሰ፡ እፍልጥ ብእሴ፡ እምአቡሁ፤ ወወለተኒ፡ እምእማ፤ ወመርዓተኒ፡ እምሐማታ፤ ወሰብአ ቤቱ፡ ይፃረሮ ለሰብእ። ዘያፈቅር አባሁ፥ ወእሞ፡ እምኔየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ። ወዘያፈቅር ወልዶ፥ ወወለቶ፡ እምኔየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ። …ዘይመጽእ ኀቤየ፥ ወይፈቅድ ይትልወኒ፡ ለእመ ኢጸልአ አባሁ፥ ወእሞ፥ ወብእሲቶ፥ ወቤቶ፥ ወውሉዶ፥ ወአኀዊሁ፣ ወአኃቲሁ፥ ወዓዲ ነፍሶኒ፡ ኢይክል ከዊነ ረድእየ። ወዘኢይፀውር መስቀሎ፥ ወኢይመጽእ ይትልወኒ፡ ኢይክል ከዊነ ረድእየ። …ኵሉ ዘእምኔክሙ ዘኢወጽአ እምኵሉ፥ ወዘኢይትናከር ኵሎ ዘዚአሁ ንዋየ፡ ኢይክል ከዊነ ረድእየ። …ዘኢያጥብዐ፥ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞቱ፥ ወዘኢተለወ ድኅሬየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ።”

ማለትም፡ “በእኔና በቃሌ የሚያፍር ኹሉ፡ የሰው ልጅ፡ በክብሩ፥ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱም ክብር ሲመጣ፡ በእርሱ ያፍርበታል። ...ስለዚህ፡ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት ባለው፡ በአባቴ ፊት እክደዋለሁ። በምድር ላይ፡ ሰላምን ለመስጠት፡ የመጣሁ አይምሰላችሁ! መለያየትን፥ ሰይፍን እንጂ፡ ሰላምን ለመስጠት አልመጣሁም። ሰውን፡ ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም፡ ከእናቷ፥ ምራትንም፡ ከአማቷ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰውም፡ ቤተሰቦቹ፡ ጠላቶች ይኾኑበታል። ከእኔ ይልቅ፡ አባቱን፥ ወይም እናቱን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም፡ ወንድ ልጁን፥ ወይም ሴት ልጁን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም። ...ማንም፡ ወደእኔ የሚመጣ ቢኖር፡ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንም፥ ልጆቹንም፣ ወንድሞቹንም፣ እኅቶቹንም፥ የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም። ማንም፡ መስቀሉን ተሸክሞ፡ በኋላዬ የማይመጣ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም።...ከእናንተ ማንም፡ ያለውን ኹሉ የማይተው፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም። ...የመስቀሉን ሞት ተሸክሞ፥ በኋላዬም ጨክኖ የማይከተለኝ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም። ነፍሱን የሚያገኝ፡ ያጠፋታል፤ ነፍሱን፡ ስለእኔ የሚያጠፋ ያገኛታል። ” (ሉቃ. ፱÷ ፳፫-፳፮፤ ፲፪÷ ፵፱-፶፫፤ ፲፫÷ ፳፫-፴፤ ፲፬÷ ፳፮-፴፫። ማቴ. ፯÷ ፲፫-፲፬፤ ፲÷ ፴፪-፴፱።)

፬ኛ፡- የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን በሚመለከት፡ በእነዚህና በሌሎቹ አያሌ የእግዚአብሔር ቃላት መሠረት፡ ለእያንዳንዳችን ምእመናን የተሰጠን፡ የኃላፊነትና የባለአደራነት ድርሻ፡ እንደባለመክሊቶቹ ኹሉ፡ ይነስ ይብዛ እንጂ፥ በምንም መሥፈሪያ፡ ከባለአንዲቱ መክሊት ሊያንስ አይችልም፤ ስለዚህ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ የየራሳችንን ምርጫና ውሳኔ ከሚጠይቅና ከሚጠብቅ በቀር፡ እንኳንስ ከሰው፡ ከፈጣሪም፡ የሚጠበቅ፡ አንዳችም የቀረና የሚታገዝ ነገር ከቶ የለም።

በዚህ ረገድ፡ እኔና ቤተሰቤ፡ እያካኼድነው ባለነው ተልእኮ ላይ፡ ከያግጣሚው እየደረሰ ያለውን የተውቃሞ ዘመቻ ስለማውቀው፥ እርስዎም፡ አፍአዊዉን፡ በመጠኑም ቢኾን፡ እየተመለከቱ ስለሚገነዘቡት፡ በጊዜያችን፡ ከዚያ የቀረበ ድርጊትንና ኹኔታን፡ በእርግጠኛ ምሳሌነትና ማስረጃነት፡ ላቀርብልዎ ያዳግተኛል።

ታዲያ፡ እኛ፡ በዚያው በጀመርነው፥ በተያያዝነውና በተከተልነው መንገድ ለመቀጠል የቻልነው በምን መሰለዎ? በዚሁ፡ በጌታ መመሪያና ማስጠንቀቂያ አይደለምን? ነው እኮ! ይህንኑ ተልእኮ፡ እኔና ቤተሰቤ፡ በመጀመሪያ፡ በየራሳችን ፍላጎትና ፈቃድ በመምረጣችን፥ ቀጥሎ፡ ያን ምርጫችንን፡ በተግባር ልንፈጽመው በመወሰናችን፥ በመጨረሻም፡ ያን ምርጫችንንና ውሳኔያችንን፡ በሥራ ላይ አውለን፡ ለፍሬ ለማብቃት በምንችልበት፥ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከፈጣሪው፡ በተፈጥሮና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተሰጠው፡ የሃይማኖትና የእውቀት ኃይል በመጠቀማችን ነው። የእርስዎም ፍላጎትና ምርጫ፡ ይህ፡ እኛ፡ አኹን፡ በምግባርዎ ተከሥቶ፡ በአንክሮና በተዘክሮ የምንመለከተውና የምንከታተለው ከኾነ፡ በዚህ የሃይማኖትና የምግባር አቋምዎ ምክንያት፡ እርስዎንም፥ ቤተሰብዎንም የሚጠብቃችሁ ጽዋ፡ ከዚህና ከቀረው የጌታ መለኮታዊ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ውጪ ሊኾን፡ ከቶ አይችልም።

፫ኛ፡- በደብዳቤዎ ውስጥ፡ *“የተራው ካህን ክህነትም፡ በዚህ ምክንያት ይሻራልን? ኅብስቱን [እና ወይኑን]፡ ወደሥጋና ደም መለወጥ አይችልምን? ካልቻለስ፡ የት ኼደን እንቍረብ? ቍርባን ቆሟልን?”* ብለው ላቀረቧቸው ጥያቄዎችዎ፡ ከላይ ቀደም ብሎ ከተሰጠው መልስ ጋር የተያያዘውንና ከዚያ የቀረውን፡ ከዚህ በታች፡ በተጨማሪ ልገልጥልዎ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፡-

ከመጻሕፍቱና ከሌሎቹ ድርሰቶቹ ከተረዱት ጋር፡ በተለይ፡ በቅርቡ፡ በጎዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ ወጥቶ ከሚነበበው፡ “የምሥራች!” የሚል ርእስ ካለው መልእክት እንደተመለከቱት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የሚያምን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ የጾታ ልዩነት ሳይከለክለውና ሳይወስነው፡ በተለይ፡ በመጀመሪያው፥ በመካከለኛውና በመጨረሻው መልከ ጼዴቆች አብነትና አማካይነት፡ የእግዚአብሔር ልጅና የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ፡ ንጉሥ/ንግሥት፥ ካህንም ነው። ይህ ክብርና ጸጋ የተሰጠውና የተረጋገጠለት፥ የታተመለትም፡ ሥርዓተ ጥምቀቱን በፈጸመበት፥ ቅዱሱን ቅብዓት በተቀባበትና ቅዱስ ቍርባንን በተቀበለበት፡ በ፵ኛው/በ፹ኛው የሥጋ ልደቱ ቀን ነው፤ ማለትም፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሔር፡ እንደገና በተወለደበት፥ ይህን ልጅነቱን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ፡ በከበረበትና በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ባተመበት ዕለት ነው።

ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ፡ ይህ ሰብአዊ ፍጡር፥ ይህ ሕፃን፡ በዚያ የእግዚአብሔር ልጅነቱ፥ በዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽነቱ፤ ማለትም፡ በንግሥት/በንጉሥነቱና በካህንነቱ፡ ይቀጥላል፤ ሌላ ሥርዓት አያስፈልገውም።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ይህ ሰብአዊ ፍጡር፥ ይህ ሕፃን፡ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ፡ ቀደም ብሎ፡ በእግዚአብሔር መልክ የመፈጠሩንና "ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" የተባለበትን፡ ደጉንና ክፉውን ያወቀበትን፡ ፍጹሙን እግዚአብሔራዊ እውቀት፡ የመቀዳጀቱን ክብርና ጸጋ በማጽናት፡ ራሱ ኹለንተናው፡ ዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት የተጻፉበት ጽላትና የዚያ ጽላት ማደሪያ ታቦት፥ የዚያ ታቦት መቀመጫ መንበርና የዚያ መንበር ማረፊያ መቅደስ ይኾናል። ይኼ የተቀደሰ ሰውነቱ የሚኖርበት ቤቱም፡ ቤተ ክርስቲያን ይኾናል።

እንግዴህ፡ ፈጣሪያችን፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ የሰጠው ጸጋና ያቀዳጀው ክብር፡ ይህን የመሰለውንና ቀና የኾነውን የመፍትሔ መመሪያ ነው። በዚህ፡ መሠረት፡ እርስዎና እኔ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዚህ ረገድ የገጠመንን ችግር፡ ለማስወገድ፡ ምንም ዓይነት እንቅፋት ሳይኖርብን፥ ወይም፡ ምንም ዓይነት ምክንያት መፍጠር ሳያስፈልገን፡ በቀጥታና በቀላሉ ልናስወግደው እንድንችል አድርጎልናል።

ይኸውም፡ እንዲህ በሚል፡ ሦስት ማማረጫ ባለው መንገድ ሊፈጸም ይችላል፤ ይህንም፡ ከዓመታት በፊት፡ አለቃ አያሌው ታምሩ የተባሉት፡ "የደርግ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት ሰው"፡ ከዛሬዎቹ፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" መሪዎች ጋር፡ በሥልጣንና በጥቅም ተጣልተው፡ በተለዩ ጊዜ፡ ለተከታዮቻቸው ባስተላለፉት የውግዘት ቃል ምክንያት፡ ለተፈጠረው ችግር ማስወገጃ የሚረዳ፡ የመፍትሔ አሳብ አበረክታቸው ዘንድ፡ ከምእመናን ለቀረበልኝ ጥያቄ፡ የሰጠሁት መልስ ነበር፡-

አንደኛው ማማረጫ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ፥ ምግባሩና ሥርዓቱ፡ ታማኝ ኾኖ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብና ቤተ ምልክና ብቻ ሳይኾን፡ በቤተ ክህነቱ ጭምር፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፥ ምግባርና ሥርዓት ላይ፡ እየተፈጸመ ባለው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ተካፋይ ሳይኾን፡ ራሱን፡ ከዚህ ታላቅ ኃጢአትና በዚሁ ምክንያት እየወረደ ካለው የመለኮታዊው ውግዘት መቅሠፍት ነጻ ያደረገ ካህን ካለ፡ ከእርሱ፡ ክህነታዊ አገልግሎትን መቀበል፤

ኹለተኛው ማማረጫ፡ ይህን የመሰለ ካህን ካልተገኘ፡ ከላይ እንደተብራራው፡ የቍጣውና የመቅሠፍቱ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ፡ እያንዳንዳችን፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብተን ባገኘነው፡ የልጅነት፥ የክህነትና የምልክና ጸጋና በረከት፥ ኃይልና ክብር በመጠቀም፡ **"ሑር ሕዝብየ፥ ወባእ ቤተከ፤ ወዕጹ ኆኅተከ፤ ወተኀባእ ኅዳጠ ምዕረ፤ እስከየኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር።" ማለትም፡ "ሕዝቤ ሆይ! ና! ወደቤትህም ግባ! ደጅህን በኋላህ ዝጋ! ቍጣ እስኪያልፍ ድረስ፡ ለጥቂት ጊዜ ተሸሸግ! በምድር በሚኖሩት ላይ፡ በበደላቸው ምክንያት፡ ቍጣውን ያመጣባቸው ዘንድ፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ ከሥፍራው ይወጣል።"** በሚለው፡ መለኮታዊ መመሪያ መሠረት፡ ከላይ በተብራራው፡ በየራሳችን የክህነት ሥልጣንና በሰውነታችን ታቦትነት፥ በየቤታችንም ቤተ ክርስቲያንነት እየተገለገልን መቆየት፤ (ኢሳ. ፳፮፥ ፳-፳፩።)

ሦስተኛው ማማረጫ፡ ምናልባት፡ እነዚህ ኹለት ምርጫዎች የማያረኩን ኾነው ከተገኙ፥ ከእነዚህ ይልቅ፡ ካህናትና ምእመናን ወደሚሰበሰቡባቸው አብያተ ክርስቲያናት የመኼድ ፍላጎት ካደረብን፡ እንኳንስ፡ የራሴ ወደሚኳት ቀርቶ፡ ወደሌሎችም ቢኾን፡ መኼድና ሥጋ ወደሙን መቀበል ይቻላል። ምክንያቱም፡ የእኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አምልኮ የሚካኼደው፡ <u>"በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ"</u> በመኾኑ፡ ወደዚያ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ኼደን የምንሰግደው ስግደትና የምንጸልየው ጸሎት፡ እግዚአብሔር የሚቀበለው ስግደትና ጸሎት የሚኾነው፥ የምንቀበለውም ቍርባን ተለውጦ፡ የመለኮት ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የሚኾነው፡ በእያንዳንዳችን እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ ሃይማኖትና ምግባር መኾኑን አምነን ስለምንፈጽመው ነው።

ይህንንም እውነታ፡ በውዳሴና በቅዳሴ ማርያም ትርጓሜዎች ላይ፡ **"ካህናቱ የበቁ ኾነው፡ ምእመናኑ ያልበቁ ከኾኑ፡ መልአኩ፡ የምእመናኑን ወስዶ፡ ለካህናቱ ያቀብላቸዋል፤ ምእመናኑ የበቁ ኾነው፡ ካህናቱ ያልበቁ ከኾኑ፡ መልአኩ፡ የካህናቱን ወስዶ፡ ለምእመናኑ ያቀብላቸዋል፤ ካህናቱም ምእመናኑም ያልበቁ ከኾኑ፡ መልአኩ፡ የካህናቱንም፥ የምእመናኑንም ወስዶ፡ በውጭ፥ በበረሃም ላሉት ለበቁት ያቀርብላቸዋል።"** ተብሎ የሚነገረው ሓተታ ያረጋግጠዋል።

፯ኛ፡ ***"የእርስዎ [የጽሑፍ ማስረጃዎች] ምንጭ፡ ከየት ነው?"*** ብለው ለጠየቁኝ፡ የምሰጥዎ መልስ፡ እንዲህ የሚል ነው፦

ለዚህና ለሌሎቹ፡ በዚህ ደብዳቤዎ ውስጥ ለተጠቀሱት ጥያቄዎችዎ፥ እንዲሁም፡ ከዚህ ውጭ ለኾኑት፡ እንዲሁም፡ በመጻሕፍቴና በጎዋ ሰሌዳችን ላይ ለተላለፉት፥ ወደፊትም ለሚተላለፉት መልእክቶች፡ ዋቢ አድርጌ የምጠቅሳቸው፡ ሰው-ሠራሽ ምንጮች የሉኝም።

ያማ ከኾነ፡ እያደረስሁ ያለሁት መልእክት ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ሳይኾን፡ እንደሌሎቹ ሰብአውያን ድርጊቶች፡ "የሰዎችን መልእክት ይኾናል!" ማለት ነው። ደግሞስ፡ ለእግዚአብሔር እውነት፡ ምስክርና ማስረጃ፥ ማጠናከሪያም ኾኖ የሚቀርበው የሰዎች ሥራ ሊኾን ይገባልን? አይገባም፤ ሊኾንም አይችልም።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በኩል ስለተላለፉትና ስለሚተላለፉት መልእክቶች ኹሉ፡ ምንጫቸውን ማሳወቅና መግለጽ ካስፈለገ፡ የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሃይማኖታዊና ምግባራዊ አቋም፡ "የኹሉ መሠረት፥ መነሻና ምንጭ፡ <u>ራሱ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ</u> ነው።" በሚል ቃል ይጠቃለላል። እርሱም ሲተነተን፡ "የእግዚአብሔር ህልውና፥ የእውነቱና የመንግሥቱ፥ የሥርዓቱና የሥራው፡ ሕያው መዝገብና ሓውልት፥ መገለጫና ቀላጤ፡ ጥንቱኑ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውና ከዚህ የተነሣ፡ የእግዚአብሔርን እውቀት የታደለው፥ በመጨረሻም፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ የኾነው፡ ሰው (ወንድ ኾነ ሴት) ነው።" ተብሎ ይብራራል።

ይህም ይታወቅ ዘንድ፡ "ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ንግበር ሰብአ፡ <u>በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ!</u>' ...ወገብሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው፤ <u>በአምሳለ እግዚአብሔር</u>፤ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ፡። ...ወይቤ እግዚአብሔር፤ 'ናሁ አ<u>ዳም፡ ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ</u>! ያእምር ሠናየ ወእኩየ!"

ማለትም፡ "እግዚአብሔርም አለ፡- 'ሰውን፡ <u>በመልካችን፥ እንደምሳሌያችን</u> እንፍጠር!' ...እግዚአብሔርም፡ ሰውን፡ <u>በመልኩ</u> ፈጠረ፤ <u>በእግዚአብሔር መልክ</u> ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ...እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- 'እነሆ፡ <u>አዳም</u>፡ መልካምንና ክፉን ለማወቅ፡ <u>ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ</u>!' የሚለው መለኮታዊ ቃልና ጸጋ፡ የመጀመሪያው የኪዳነ ልቦና ምንጭ ነው።

የመካከለኛው የኪዳን አሪት ምንጭ ደግሞ፡ "ወኵሎሙ ደቂቅኪ፡ ምሁራን፡ በኀበ እግዚአብሔር። '...ወእምድኅረ እማንቱ መዋዕል፥' ይቤ እግዚአብሔር፣ 'እወዲ ሕግየ ውስተ ልቦሙ፤ ወእጽሕፎ ውስተ ሕሊናሆሙ። ወእሬስዮሙ እንከ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ። ወአልቦ ዘይሜህር እንከ አሐዱ አሐዱ እኅዋሁ፤ ወአሐዱ አሐዱ ቢጾ፤ ወይብሎ፡- ‹አእምሮ ለእግዚአብሔር!› እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፣ ንኡሶሙ፣ ወዐቢዮሙ።' ይቤ እግዚአብሔር።"

ማለትም፡ "...ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ። '...ከዚያ ወራት በኋላ፡' ይላል እግዚአብሔር፡ 'ሕጌን በልቡናቸው አሳድራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እንግዴህ ወዲህም፡ እንዲጠብቁት አደርጋቸዋለሁ፤ እኔ፡ የፍቅር አባት እኾናቸዋለሁ፤ እነርሱም፡ የፍቅር ልጆቼ ይኾኑኛል። ከዚህ በኋላ፡ አንዱም አንዱ፡- ‹እግዚአብሔርን እወቅ!› ብሎ ወንድሙን የሚያስተምር፣ አንዱም፡ አንዱ፡ ባልንጀራውን የሚያስተምር የለም፤ ታናሹም፥ ታላቁም ኹሉ፡ እኔን ያውቁኛልና፤' ይላል እግዚአብሔር።" የሚለው፡ የነቢያት ቃል ነው።

የመጨረሻው፡ የኪዳን መንፈስ ቅዱስ የመደምደሚያ ምንጭም፡ "እፎ የአምር ዝንቱ፡ መጽሐፈ፡ ዘኢመሃሮ መኑሂ?!" ማለትም፡ "ይህ ሰው ሳይማር፡ መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል?" ብለው፡ በመደነቅ፡ እርስ በርሳቸው ለተጠያየቁት አይሁድ፡ "ትምህርትየሰ፡ ኢኮነት እንቲአየ፤ አላ፡ እንቲአሁ ለዘፈነወኒ።" ማለትም፡ "ትምህርቴስ፡ ከላከኝ ነው እንጂ፡ ከእኔ አይደለም!" ሲል፡ መልስ የሰጣቸው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እነዚህን የቀደሙትን ምንጮች መሠረት በማድረግ፡ የተናገረው፡ እንዲህ የሚለው፡ የማኅተም ቃል ነው፡-

"ወሀሎ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሐፈ ነቢያት፡ 'ከመ ይከውኑ ኵሎሙ ምሁራነ፡ እምኀበ እግዜብሔር።' ወኵሉ እንከ፡ ዘሰምዐ፡ በኀበ አቡየ ተምሂሮ፡ ይመጽእ ኀቤየ።" ማለትም፡ 'ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!' ተብሎ፡ በነቢያት ተጽፏል:: እንግዲህ፡ ከአብ የሰማ፥ የተማረም ኹሉ፡ ወደእኔ ይመጣል።"

ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ በዚህ ረገድ፡ በግለሰብ አማኞች ላይ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል፡ እየተፈጸመ የቀጠለውን፡ ዕፁብ ድንቅ ኹኔታ ደግሞ፡ ለዓይነት ያህል፡ በጥቂቱ የጠቀስኋቸው፡ ከዚህ የሚከተሉት ቃላት ያስረዳሉ፡-

በመጀመሪያ፡ ሐዋርያትን፡ በሸንጎ አቁመው፡ “አኮኑ ከላእናክሙ፡ ከመ ኢትምሀሩ፡ በስሙ፡ ለኢየሱስ፥ ወኢለመኑሂ? ወናሁ መላእክምዋ ትምህርተክሙ ለኢየሩሳሌም፤” ማለትም፡ “በዚህ [በኢየሱስ ክርስቶስ] ስም እንዳታስተምሩ፡ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆ፡ ኢየሩሳሌምን፡ በትምህርታችሁ ሞልታችኋል፤” ብለው የጠየቋቸው፡ የአይሁድ ሕዝብ ሽማግሌዎች፥ የካህናት አለቆችና ጻፎች፡ “ወሶበ ርእይዎሙ ለጴጥሮስ፥ ወለዮሐንስ፡ ከመ ገሃደ ይነግርዎሙ፡ አእመርዎሙ፡ ከመ ሰብእ የዋሃን እሙንቱ፤ ወኢያአምሩ መጽሐፈ፤ ወአንከርዎሙ።” ማለትም፡ “ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ በግልጥ እንደተናገሩ ባዩ ጊዜ፡ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደኾኑ አስተውለው አደነቁ።”

ኹለተኛም፡ “እምጳውሎስ ሐዋርያ፡ ዘኢኮነ፡ በእንተ ሰብእ፤ ወኢኮነ፡ እምኀበ ሰብእ፣ ዘእንበለ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወእግዚአብሔር አብ፡ ዘአንሥኦ እሙታን።” ማለትም፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከሙታንም ለይቶ ባነሣው፡ በእግዚአብሔር አብ፡ ሐዋርያ የኾነ እንጂ፡ ከሰዎች፥ ወይም ከሰው ባልኾነ ከጳውሎስ!” በሚል መግቢያ፡ ራሱን በማስተዋወቅ፡ የመልእክቱን ጽሑፍ የከፈተው፡ ስመ ጥሩውና ባለሙያው ሐዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ የመልእክቱን ጽሑፍ በመቀጠል፡ “እነግረክሙ አኀዊነ፡ እስመ ትምህርት ዘመሀርኩክሙ፡ ኢኮነ፡ በእንተ ሰብእ። ወአነሂ፡ አኮ እምኀበ ሰብእ ዘነሣእክዎ፤ ወኢሂ መሀሩኒዮ፤ ዳእሙ፡ በዘከሠተ ሊተ፡ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ።” ማለትም፡“ወንድሞች ሆይ! በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ። እኔ፡ ከሰው አልተቀበልሁትም፤ አልተማርሁትምም።” (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፯፤ ፫፥ ፳፱። ኢሳ. ፶፬፥ ፲፫። ኤር. ፴፩፥ ፴፫-፴፬። ዮሐ. ፮፥ ፵፭፤ ፯፥ ፲፭-፲፮። የሐዋ. ፬፥ ፲፫፤ ፭፥ ፳፰። ገላ. ፩፥ ፩-፲፱። ዕብ. ፰፥ ፰-፲፱።)

እንግዴህ፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የቅዱሱ ኪዳን ህልውናቸው ከጀመረበት፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ፡ መርጠው የተቀበሉት ሃይማኖታዊ እውቀታቸውና እንደነቢያት፡ በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ የሚኖሩበት ምግባራዊ ሥርዓታቸው፡ ባጭሩ፡ ይህ፡ በእግዚአብሔር ቃላት እየተደገፈ፡ ከዚህ በላይ የተገለጠው ነው።

የጽሕፈት ምስክርነት፡ ለእግዚአብሔር እውነትና የሕይወት ህልውና የሚበጅና የሚጠቅም፥ የሚያስፈልግም የእውቀት ምንጭ ቢኾን ኖሮ፡ ፈጣሪያችንና ጌታችን፥ መምህራችንና ሊቃችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አያሌ መጻሕፍትን ትቶልን ባረገ ነበር። ከዚህ ይልቅ፡ በዚህ ረገድ፡ ጥንት፡ በፍጥረት መጀመሪያ የሠራውና በነቢያት ያሳየው፥ በመካከሉም፡ ራሱ ሰው ኾኖ መጥቶ የነገረንና ያስተማረን፥ በምድርም ላይ ትቶልን ያረገው፥ ኋላም በመንፈስ ቅዱስ የገለጠልን፡ "መንፈስ ውእቱ፡ ዘየሐዩ፤ ወሥጋስ፡ አልቦ ዘይበቍዕ፤ ወኢምንተኒ። ወዝኒ ቃል፡ ዘአነ ነገርኩክሙ፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወሕይወት ውእቱ።" ማለትም፡ "ሕይወትን የሚሰጥ፡ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም። እኔ፡ የነገርኋችሁ ቃል፡ መንፈስ ነው፤ ሕይወትም ነው።" የሚለውን እውነታ ብቻ ነው። (ዮሐ. ፮፥ ፷፫።)

አንዱ ሐዋርያም፡ ይህን መለኮታዊ የእውነት ቃል በመከተልና በማጽናት፡ የእግዚአብሔር የጽሕፈት መልእክት ማስተላለፊያ ክርታስና ማኖሪያ መዝገብ፡ የሰው ሕያው አካል መኾኑን፥ የሰዎች የጽሕፈት ቅርስና ውርስ ግን፡ ሙሉ እምነት ሊጣልበት የማይቻል፥ ስሑት እንጂ እሙን፥ ገዳይ እንጂ ማሕየዊ አለመኾኑን፡ አብራርቶ በመግለጽ፡ እንዲህ ሲል ያመለከተውን ቍም ነገር፡ እዚህ ላይ ጠቅሼዋለሁ፡-

"ወለነሰ፡ መጽሐፍነ፡ አንትሙ ይእቲ፤ ወጽሕፍት ውስተ ልብነ፤ ወትትዐወቅ፤ ወያነብባ ኵሉ ሰብእ። ወየአምሩክሙ፡ ከመ መልእክተ ክርስቶስ አንትሙ፣ እንተ ተልእክናሃ ንሕነ። ወጽሕፍት ይእቲ፣ ወአኮ በማየ ሕመት፣ ዘእንበለ በመንፈሰ እግዚአብሔር ሕያው፤ ወኢኮነ ጽሌ ዘእብን፣ ዘእንበለ ጽሌ ልብ፡ ዘሥጋ። ወብነ ባሕቱ፡ ከመዝ ተስፋ፡ በኀበ እግዚአብሔር፡ በእንተ ክርስቶስ። ወኢይደልወነ ነሐሊ፡ ለሊነ ለርእስነ፡ ወኢምንተኒ፤ እስመ እምኀበ እግዚአብሔር ኃይልነ፣ ዘረሰየነ ላእካነ፡ ለሐዲስ ሕግ፤ ወአኮ፡ በሕገ መጽሐፍ፤ አላ፡ በሕገ መንፈስ፤ እስመ መጽሐፍ ይቀትል፤ ወመንፈስ የሐዩ።"

ማለትም፡ "ሰዎች ኹሉ፡ የሚያውቁትና የሚያነብቡት፡ በልባችን የተጻፈ መልእክታችን፡ እናንተ ናችሁ። እናንተም፡ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ፡ በቀለም ያይደለ፥ ሥጋ በኾነ፡ በልብ ጽላት እንጂ፡ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ፡ የክርስቶስ መልእክት እንደኾናችሁ የተገለጠ ነው። በክርስቶስም በኩል፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ እንዲህ ያለ ተስፋ አለን።

"ብቃታችን፡ ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፡ በገዛ እጃችን እንደሚኾን፡ አንዳችን እንኳ ልናስብ፡ ራሳችን፡ የበቃን አይደለንም፤ እርሱም ደግሞ፡ በመንፈስ እንጂ፡ በፊደል ለማይኾን፡ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና፤ መንፈስ ግን፡ ሕይወትን ይሰጣል።" (፪ቆሮ. ፫፥ ፪-፮።)

፮ኛ፡ በደብዳቤዎ ውስጥ፡ *"ከተለመደው ታሪክ ወጣ ያለ ነገር ሲተረክ፡ በብዙኃኑ ላይ የሚፈጠረውን ስሜት በሚገባ ያውቁታል።"* ላሉት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተውንና የጸናውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን መልእክት፡ "ብዙኃኑን" ሳንፈራና ሳናፍር፥ ይሉኝታቸውም ሳይበግረን፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በይፋ ገልጠንና በድፍረት ቀርበን የማናደርስ ከኾንን፡ እውነቶች አገልጋዮች አለመኾናችንን፡ እንኳንስ በፈጣሪያችን ዘንድ፡ በሰዎች ዘንድ ሳይቀር፡ ማረጋገጣችን አይኾንምን? አዎን! ይኾናል።

"ይረትዕኑ በቅድመ እግዚአብሔር፡ ኪያክሙ ንስማዕ፤ ወአኮ ለእግዚአብሔር? ፍትሑ፡ እስኩ ለሊክሙ። ንሕነሰኬ፡ ኢንክል ከቢቶቶ ለዝንቱ ነገር። ...ይኄይሰነ ናድሉ ለእግዚአብሔር፡ እምነ አድልዎ ለሰብእ።" ማለትም፡ እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ፡ እናንተን እንሰማ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደኾነ ቍረጡ! እኛስ፡ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር፡ ዝም ማለት አንችልም። ...ከሰው ይልቅ፡ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።" የሚለውንም፡ የሓዋርያትን ቃል ማስተሓቀር ይኾናል። የየራሳችን ኀሊናም ይታዘበናል።

ወንጌላዊው ዮሓንስ፡ ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ የጻፈው፡ እንዲህ የሚለው ኃይለ ቃል፡ አግባብነት ስላለው፡ እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይገባዋል፡- "ወቦ ብዙኃን፡ እመላእክተ ሕዝብ፡ እለ አምኑ ቦቱ [በኢየሱስ ክርስቶስ]፤ ወባሕቱ፡ ኢያግህዱ፡ በእንተ ፍርሃቶሙ ለፈሪሳውያን፣ ከመ ኢይስድድዎሙ፡ እምነ ምኲራብ፤ እስመ አብደሩ፡ ስብሓተ ሰብእ፡ ፈድፋደ፡ እምስብሓተ እግዚአብሔር።" ማለትም፡ "ከአለቆች ደግሞ፡ ብዙዎች፡ በእርሱ [በኢየሱስ ክርስቶስ] አመኑ፤ ነገር ግን፡ ከምኲራብ እንዳያስወጧቸው፡ በፈሪሳውያን ምክንያት፡ አልመሰከሩለትም፤ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ፡ የሰውን ክብር ወድደዋልና።" (የሓዋ. ፬፥ ፲፱፤ ፭፥ ፳፱። ዮሓ. ፲፪፥ ፵፪-፵፫።)

"በጉጉት እጠባበቀዋለሁ!" ያሉትን መልሴን፡ መንፈስ ቅዱስ ባመለከተኝ፥ እኔም በተገነዘብሁት መጠን የገለጥሁልዎትን ሓተታ፡ እነሆ፡ እዚህ ላይ እገታለሁ።

## ከወ/ሮ ፍቅርተ የተላከ፡ ኹለተኛ እ-ጦማር፤

I thank you very much for the explanations on my questions. Now it makes sense. Though it is a lot to reconcile, misunderstandings are the result of defining things narrowly. Understanding the begining of the Ethiopian race for the third time by Melchizedek is misleading unless one sees the big picture.

And I also felt relief when I read about your explanation regarding authenticity of Church service. Well, we can't do anything except doing what we can do. So, I will keep on partaking the service counting on God's mercy on me and His servants. Worshipping God in spirit with out dependence on congregations is... for me... a very difficult thing to imagine in my present level of spiritual development. It needs the activation of the inner temple in one's own spirit, which has the Ark and the Shrine and the Word of God and everything.... I have many onion layers to peel and many curtains to unveil until I reach there. Hopefully I can get there, and probably it is closer than I thought. But thanks for letting me and all your other readers to to know that our destiny is ultimately with in our own spirit.

I say "Egziabher yistilign" once again from the bottom of my heart for all the enlightening messages you have so far helped me to get. I strongly believe that one day the idea of Ethiopiawinet will be my full time cause.

I have a question again.... when is "Adam ena Hewan be ItyoPya" going to be published? Is that basically the same content that you published as "Ethiopia ena Ethiopiawinet" qutir 1, 2, & 3; or is it a different book having other contents?

## ለዚህ፡ ለኹለተኛው እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

**ለወ/ሮ ፍቅርተ፡-**

በደርግ እሥር ላይ በነበርሁበት ጊዜ፡ የጻፍኋቸውን ሦስት ተከታታይ መጻሕፍት በሚመለከት፡ በዚህ፡ የመልስ እ-ጦማርዎ መዝጊያ ላይ ላቀረቡልኝ ጥያቄ፡ የምሰጥዎ መግለጫ፡ እንደሚከተለው፡ አጭር፡ ነው፡-

"አዳም እና ሔዋን በኢትዮጵያ።" በሚል ዐቢይ ርእስ ሥር፡ በደርግ እሥር ቤት ሣለሁ ያዘጋጀኋቸው፡ እነዚያ መጻሕፍት፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚል አርእስት፡ በአኹኑ ጊዜ ታትመው የተሠራጩትና በእርስዎም እጅ የሚገኙት፡ ሦስት ተከታታይ መጻሕፍት አይደሉም፤ ሌሎች ናቸው። እነርሱም፡ ፩ኛ፡ "በጦቢያ ፍለጋ!"፥ ፪ኛ፡ "በእውነት ፍለጋ!" እና ፫ኛ፡ "በእውቀት ፍለጋ!" የሚል ንዑሳን አርእስት ያላቸው ናቸው።

እነዚህ መጻሕፍት፡ በእናትና ልጇ ፈቃድ፡ የመቀመሪያ ዝግጅታቸው ተራ ደርሶና ተጠናቅቆ፡ ሩቅ ባልኾነ ጊዜ ውስጥ፡ ለማኅተምና ለሥርጭት እንደሚበቁ ተስፋ አደርጋለሁ።

## ከወ/ሮ ፍቅርተ የተላከ፡ ሦስተኛ እ-ጦማር፤

I know that I am a bit impatient regarding emailing questions and then waiting for response. After the last long and thoughtful letter of yours, I have understood that I am taking your time for things that I am failing to understand because of lack of insightful reading of your books. And forgive me for that.

Anyway,... I am now back with another question. (I can't help, but come back) This time, I can't get the answer from your books that are with me now. That is why I am emailing.

I have contacted my friends and a couple of times we have raised about the issues of your service. It is very discouraging that people seem to investigate personal stories instead of what is put infront of them. So, they have kept asking me "Nibure-Id has ordained his wife as a priestess and performed liturgy with her on his son's wedding in Bahir Dar. So, are you still following his books and teachings?" I insisted on asking them to tell me if they have seen any wrong idea in the books, and of course, they have nothing to say. Some of the previous reactions were even sarcastic. But, I would like to keep having a serious discussion with some of the people that I think are open minded, and make my stand clear for myself in this moment that is chaotic for everyone of us (the chaos of the synod issue and the resultant dis-orientation that EOTC affiliated societies are currently in).

So, my question is simple; have you ordained Kib’rt Weizero Rahel as a preistess? And has She taken part in the liturgy performed on your Son's wedding? If yes, I know how you would justify that spiritually; of course I know St. Paul has said "ke’ingdih wedih ayhudawim yellem, Greekawim yellem, wendm yellem, setim yellem; hulu bek’r’stos 1 new enji"; and I also remember your explanation of the side effects of excluding women from such ordinations in our discussion two years ago. But, how do you justify that in terms of canonical decisions? Is it the case that, you, as the accountable body (representative- "teTeri") of Ethiopia Kingdom of God Services, decided to include this as a canon by the spiritual authority vested upon you by EKOG? Or is it an emergency-case service provided by Weizero Rahel on that day, and not a full ordination as a preistess?

I actually think what I heard is a lie, because, if it were true, I could have seen "Preistess Rahel" somewhere in your website or the article about the marriage issue ("be Qidusu Kidan ItyoPyawinet tsento megegnet endet chink newu?" yemilew) . If it is not a lie, then I would have to open my understanding for further accomodation of new knowledge about Ethiopia Kingdom of God (that women can serve and are serving as preists in Ethiopia KOG) and raise my confidence level on this issue to stand firm on any question raised againist it.

Waiting for your response eagerly,

## ለዚህ፡ ሦስተኛ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

ለወ/ሮ ፍቅርተ፡-

ወደዋናው ጥያቄዎ ገብቼ፡ ተገቢውን መልስ፡ እንደሚከተለው አቀርብልዎታለሁ፡-

፩ኛ፡ በባሕር ዳር ከተማ፡ በተካኼደው፡ በሙሽራው ልጃችን እና በሙሽሪት እጮኛው፡ የሥርዓተ ተክሊልና የቅዱስ ቁርባን ሥርዓተ ቅዳሴ ሥነ በዓል ላይ፡ ባለቤቴ፡ ወይዘሮ ራሔል፡ በቅዱሳት መጻሕፍት አንባቢነት፡ ከሌሎች ጋር፡ ተካፋይ ከመኾን በቀር፡ ልብሰ ተክህኖ ለብሳ፡ በንፍቅ ቄሲስነት አላገለገለችም። ከዚህ ውጭ የተነገረው ወሬ፡ የዲያብሎስ ሓሰት ነው።

፪ኛ፡ ይህም ቢባል፡ "ወይዘሮ ራሔል፡ ሥልጣነ ክህነት የላትም!" ማለት አይደለም፤ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት፡ በዚህ ሃይማኖትና አምልኮ፥ ምግባርና ሥርዓት ጸንታ የምትገኝ ኢትዮጵያዊት፡ እርስዎም፡ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ጠቅሰው እንዳመለከቱት፡ ሥልጣነ ክህነት አላት። ይህች ሴት፡ እንደማንኛውም እውነተኛ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊና ኪዳናዊት ኢትዮጵያዊት፡ <u>በቅዱሱ ቅብዓት ተቀብታና ታትማ፡ ይህን ሥልጣነ ክህነት የተቀበለችው፡ በቀጥታ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህ የኾነውና የተፈጸመው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ከእርሱ፡ ከመለኮት፡ በውኃና በመንፈስ የተወለደችበትን፡ ኹለንተናዊ ልጅነቷን ባገኘችበትና የንግሥትነት ዘውዷን በተቀዳጀችበት፡በጥምቀቷ ጊዜ ነው።</u>

ይህች ኢትዮጵያዊት፡ ከዚህ በኋላ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ቤተ ሕዝብ ውስጥ፡ የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላት ሙሉ አባል ለመኾን፥ ከዚያም፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ፡ በሥልጣነ ክህነት፥ በቤተ ምልክናውም ውስጥ፡ በምሉክነት ሥልጣን ለማገልገል፥ ከዚህም አልፋ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ለመጨረሻው የአጼነት ማዕርግ ሊበቃ እንደሚችል ኹሉ፡ እርሷም፡ እንደማንኛዪቱ ኢትዮጵያዊት፡ ንግሥት ለመኾን፡ ብቅአቱን ስለምትጎናጸፍ፡ <u>ሌላ፡ ቅብዓት አያስፈልጋትም።</u>

በዚህ ረገድ፡ ይህች ኢትዮጵያዊት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያምም ቤተ መቅደስነትና ንግሥተ ንግሥታትነት የምትመራው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የአገልግሎት ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ ተመድባ: በመንፈሳዊዉም ኾነ በሥጋዊው አስተዳደር በኩል፡ ለማገልገል፥ በመጨረሻም፡ በተጠሪነት ዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ፡ የሚያስፈልጋት ነገር ቢኖር፡ <u>በትምህርቱና በሙያው መሠልጠን ብቻ ነው።</u>

ለዚህ፡ ለመጨረሻው የአገልግሎት ደረጃ ለመብቃትም፡ እንደሥርዓታችን፡ ለዚች ኢትዮጵያዊት የሚያስፈልጋት፡ በዚህ፡ ኹለንተናዊ ክብርና ማዕርግ ተሟልተው ከሚገኙት፡ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን መካከል፡ በእግዚአብሔር ስምና በመንፈስ ቅዱስ እውነት ተመርጣ፡ ወንዱ፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" እንደሚባል ኹሉ፡ እርሷም፡ "ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብላ፡ መስሰየም ብቻ ነው፤ እንደቀደሙት፡ ንግሥት ማክዳና ንግሥት ሕንደኬ፥ እንደቅርቧም፡ ንግሥት ዘውዲቱ ማለት ነው።

፫ኛ፡ ይህ ኹሉ፡ የክብርና የማዕርግ መለኮታዊ ጸጋ፡ ለኢትዮጵያውያት ሴቶች የተገኘው፡ ራሷን፡ ለፈጣሪ እናትነት ባበቃችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሲኾን፡ ለኢትዮጵያውያን ወንዶች ደግሞ፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ፡ በይፋ የተገለጸና የታወቀ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ የጥበብና የቸርነት ሥራ ነው።

እርስዎና እርስዎን የሚመስሉዎ፡ የእግዚአብሔርን የእውነት ፈለግ ተከትላችሁ፡ በዘለዓለማዊቷ ሕይወት ለመኖር፡ በቁርጥ ተነሣሥታችሁ የምትጋደሉ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ ሰባቱን ኪዳናት ለያዘው፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ፥ ሥርዓታችሁም፡ እየራሳችሁን በምታበቁበት ጊዜ፡ የሚጠብቃችሁ ዕድል፡ ያለጥርጥር፡ ይህ እንደኾነ፡ በተለይ እርስዎ፡ የተረዱት ይመስለኛል።

፬ኛ፡ ከዚህ በላይ የተገለጸውንና የእግዚአብሔር ሥራ የኾነውን ጸጋ፡ "ቀኖና" ከሚባለው፥ ስሑትና ሕፁፅ የኾነው የሰዎች ፈጠራ ካስገኘው ድንጋጌ ጋር ለማስማማት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት እየተመራን በምንኖረው፡ በእኛ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ በምንም መልኩ፡ የሚያሳስበንና የሚያስጨንቀን፥ የሚያስፈልገንም አይደለም፤ ምክንያቱም፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት መገለጫ ከኾነው፡ በታማኞቹ ኢትዮጵያውያን ምእመናንና ኢትዮጵያውያት ምእመናት ልቦና ላይ ከተጻፈው፥ በቅዱሳት መጻሕፍትም ውስጥ ከተመዘገበው መለኮታዊ ቃልና ግብር ጋር የማይስማማው፡ ማንኛውም ዓይነት፡ ሰው-ሠራሽ ሥርዓት፡ ሊጸና ስለማይችል፥ ፈጽሞ ፍርስና ውድቅ ኾኖ መወገድም ስላለበት ነው።

፭ኛ፡ በእ-ጦማርዎ ውስጥ፡ እርስዎም እንዳመለከቱት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያና ልጆቿ የሚኖሩባት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመራው በመንፈስ ቅዱስ ስለኾነ፡ የዚች መንግሥት አገልጋይ ኾኖ፡ ራሱን በይፋ፡ ለዚህ አገልግሎት፡ በተጠሪነት ያቀረበ ግለሰብ ቢኖር፡ ያለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ኃይል፡ ራሱን፡ ለዚህ የሰማዕትነት ተልእኮ ሊያበቃ እንደማይችል፡ የታወቀና የታመነ ነው።

ይህ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፡ ይህን የእግዚአብሔርን ሥርዓት፡ በምግባር ላይ ለማዋልና ለማወጅ፡ እንደማንኛውም እውነተኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ኹሉ፡ እርሱም፡ ይህን፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊ ሥልጣን፡ ከእግዚአብሔር እንዳገኘ፡ በታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ተቀባይነት ያለው እውነታ ነው።

፯ኛ፡ ፈጽሞ ስላልተደረገ፡ የሓሰት ወሬ የኾነው፡ ያ፡ የወይዘሮ ራሔል ክህነታዊ አገልግሎት፡ (ምናልባት ተደርጎ እንደኾነ) "ያለሙሉ ሥልጣነ ክህነት፡ ሊፈጸም የቻለው፡ በዚያች ዕለታዊ በዓል ላይ፡ የደረሰውን፡ አስቸኳይ ችግር ለማስወገድ ብቻ ተብሎ፥ እንደጊዜያዊ መፍትሔም ተደርጎ እንደነበረ መገመት ያስኬዳልወይ" በሚል ቃል ተያይዞ፡ በእ-ጦማርዎ ውስጥ የቀረበውን ጥያቄ፡ ከዚህ በላይ የተሰጠው መልስ፡ አላስፈላጊ ስለሚያደርገው፡ ነገሩ፡ በዚሁ ይቆማል።

፰ኛ፡ በመጻሕፍቴና በጎዋ ሰሌዳችን ልዩ ልዩ መድረኮች አማካይነት ከቀረቡት ጽሑፎች ጋር፡ በይበልጥ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዋናው ገጻችን ላይ ሠፍሮ በሚነበበው፡ "ምሥራች!" በሚለው መልእክት፥ በእርሱ ላይ፡ ታክሎበትና ተሟልቶ "ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።" በሚል ርእስ፡ በቅርቡ በሚወጣውም መጽሓፍ ውስጥ፡ የዚህን ጥያቄዎን ቁምነገር በሚመለከት፡ የበለጠ ግንዛቤን እንደሚያገኙ፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

## ከወ/ሮ ፍቅርተ የተላከ፡ አራተኛ እ-ጦማር፤

I am so glad to hear from you within such relatively short time as I understand that you are very busy with the service. Working on publications, family and personal committments, updating website, responding to numerous questions,... it is not easy to deal with all these, especially at this time when people like me are generally distracted and don't get the message fast enough. Look how long it took to educate me about few preliminary ideas!

So, I thank you very much for the information and explanations. They were satisfactory. I (and many other people too) tend to see Spiritual ordination and education & training for preisthood as one and inseparable. That, I think, is the root of the confusion. Thanks for clearing that up.

I really appreciate that you gave me clear and thorough response to a kind of question that I myself dislike; i.e. personal type of question. But, I would like to let you know that I am only encouraged by your own words, "le ItyoPyawi ke ItyoPyawinetu weCHi lela yegil yemibal neger yelewum" to ask the question in the first place.

I am very glad that another book is on its way to be published. I look foreward to reading it. I have no doubt it will be spiritually enightening as usual.

God bless you, your family and your service!

______________________

## ከሓኪም ትምህርተ የተላከ እ-ጦማር፤

ከእርስዎ መልስ አገኝ ዘንድ፡ የማቀርባቸው ኹለት ጥያቄዎች አሉኝ፤ እነርሱም፡ እንዲህ የሚሉ ናቸው፡-

፩ኛ. የጌታችን የጥምቀት በዓል፡ በጥር ፲፩ ቀን እንዲውል የተደረገው፡ ቀኑ ተመርጦ ነው? ወይስ፡ የአሪቱ የዳስ በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበረ ነው?

፪ኛ. የእመቤታችንን ትንሣኤ አስመልክቶ፡ ከነሓሴ ፲፮ እስከ መስከረም ፳፩ ቀን ድረስ፡ የት ቆየች? ምክንያቱም፡ ቶማስን አግኝታው፡ ስትነግረው፡ "ሓዋርያት፡ ትንሣኤዬንም፥ ዕርገቴንም፡ አላዩም!" ብላዋለች።

## ለዚህ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፡-

ለሓኪም ትምህርተ፤

የጥያቄዎችዎ መልሶች፡ ከዚህ፡ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ. የጥምቀት በዓል ዕለት፡ ጥር ፲፩ ቀን የሚውለው፡ የጥንቱን የአሪቱን ኪዳናዊ የዳስ በዓልና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሠላሳ ዓመት ዕድሜው በኋላ የተጠመቀበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ፡ የቀድሞዎቹ ወላጆቻችን ያጸኑትን ሥርዓት ተከትሎ ነው፤ እንደስቅለቱ ዕለተ ዓርብ እና እንደበዓለ-ሃምሳ (በዓለ መንፈስ ቅዱስ) ዕለተ እሑድ ማለት ነው። በዚህ ስሌት: መነሻው፡ የጌታችንና የእመቤታችን የልደታት ዕለት የኾነው፡መስከረም ፩ ቀን፡ በጥቅምት ፲፩ ለሚጀምረው የስደት ጾም እና በጥር ፲፩ ቀን ለሚውለው የጥምቀት በዓል መከታተል ትክክለኛነት ማስረጃና ማረጋገጫ ይኾናል።

፪ኛ. እመቤታችን፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ ከሙታን ተለይታ ተነሥታ፡ ልጇ፡ ከማረጉ በፊት፡ ሲያደርግ የቆየበትን ተልእኮ፡ እርሷም፡ ያንኑ ተከትላ፡ ስትፈጽም ቆይታለች፤ ያም፡ በሕይወተ ነፍስ ወዳሉት ኼዳ፥ በምድር ላይ ወደሚኖሩትም ተዘዋውራ፥ ወደኢትዮጵያም መጥታ፡ ለሚገባቸውና ለበቁት ቅዱሳንና ቅዱሳት እየተገለጠች፡ በሕይወተ ሥጋዋ ስታደርግ የነበረውን ተልእኮ እያካኼደችና ምሥራቹን እየነገረች ያሳለፈችው ጊዜ ነው። እነሆ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በደመና ተነጥቆ፡ በአየር ላይ ሲጓዝ አግኝታው፡ የቀሩት ሓዋርያት ወንድሞቹ ያላዩትን ትንሣኤዋንና ዕርገቷን፡ እንደልጇ ዕርገት፡ በአርባኛው ቀን በኾነው፡ ባረገችበት፡ በመስከረም ፳፩ ቀን ገልጣለታለች። ይህም፡ መለኮታዊው ቸርነትና ጥበብ፡ ዐቅዶና አከናውኖ ያዘጋጀው ምሥጢር ነው።

እመቤታችን፡ የልጇን በመሰለው የትንሣኤ አካሏ፡ ለአርባ ቀናት ስትገለጥላቸው የቆየችውና ከሓዋርያት የተለዩት፡ ሌሎች "ቅዱሳንና ቅዱሳት" የተባሉት የእግዚአብሔር ልጆች፡ በዚያን ጊዜ፡ በምድር ላይ፡ ሕያዋን ኾነው ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መኾናቸውን፡ ይህ እውነታ ያመለክታል።

---

## ከአቶ ዮናታን የተላከ፡ ፩ኛ እ-ጥማር፤

የእርስዎን መጽሓፎች፥ ኹሉንም ማለት ይቻላል፥ አንብቤያቸዋለሁ። ለጊዜው አኹን ያለሁት፡ ከአገር ውጭ ነው።

ስለሰብአ ሰገል የነገሩኝ፡ "አንዳቸውም፡ እንኳ፡ አይደሉም!" ሲሉ፡ ምን ለማለት እንደኾነ ስላልተረዳሁ ነው፡ ይህን የጻፍኩልዎት። እንግዲህ፡ ያለችዎትን ጊዜ እንደምንም ብለው አብቃቅተው ቢመልሱልኝ፡ ደስተኛ ነኝ።

## ለዚህ፡ ፩ኛ እ-ጥማር የተሰጠ መልስ፡-

ለአቶ ዮናታን፡-

"ሰብአ ሰገል" ከተባሉት፡ ሦስት የነገድ ወገኖች መካከል፡ አዎን! አንዳቸውም፡ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም፤ ነገር ግን፡ እያንዳንዳቸው፡ እዚያ የተገኙት፡ ከኢትዮጵያውያን በቀር፡ ሌሎቹን የምድር ወገኖች፡ ማለትም፡ ሦስቱን፡ የኖኅን ልጆች፡ እነርሱም፡- ሴምን ("ቀይ"፥ ወይም "ብጫ" የተባሉትን)፥ ካምን (ጥቁሮችን) እና ያፌትን (ነጮችን) ወክለው ነበር።

ድንግል ማርያም፥ በእርሷም በኩል፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጹሞቹ ኢትዮጵያኖች ሲኾኑ፡ ኢትዮጵያውያንም፡ በእናቲቱ ንግሥትነትና እናትነት፥ አገርነትና መቅደስነት፥ በልጇ አባትነትና ንጉሥነት፥ አምላክነትና ካህንነት እየተመሩና እየተዳደሩ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ልጆቻቸውና ዜጎቻቸው፥ አገልጋዮቻቸውና ሕዝባቸው ናቸው።

የእጅ መንሻን፥ ግብርንና ገጸ በረከትን የሚያቀርበው ደግሞ፡ የውጭው እና ባዕዱ እንጂ፡ የራስ ወገን፥ ወይም፡ ቤተሰብ አይደለም፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን በሚመለከት እንደተናገረው (ማቴ. ፲፯፥ ፳፬-፳፯)።

ከሦስቱ ሰብአ ሰገል መካከል፡ አንዱ፡ ማለትም፡ ጥቁሩ፡ "ኢትዮጵያዊ ነው!" የሚለውን የተሳሳተ ዘይቤ ያመጡት፡ የእኛን ኢትዮጵያዊነት ለማጥፋት፡ ከጥንት ጀምረው እስከዛሬ፡ እየተከታተሉ የዘመቱብን ተቃዋሚዎቻችን ናቸው። ይኸውም፡ እያንዳንዳችንን፡ "ኢትዮጵያዊ" የሚያሰኘን፥ ከዚህም የተነሣ፡ ድንግል ማርያም፡ "ኢትዮጵያዊት ናት!"፥ ከእርሷም፡ በሰውነት በመወለዱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ኢትዮጵያዊ ነው!" የሚለው እውነታ እንዲሻር ለማድረግ እንዲረዳቸው ነው።

ይህን እውነታ፡ ባጭሩም ቢኾን፡በበለጠ ላብራራልዎት፡-

የቅዱሱን ኪዳን እምነትና ቅርስ፡ ከኖኅ የተረከበው የመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ፡ ለ"ኢትዮጵያዊነት" ምንነትና ማንነት መገለጫና ለመጨረሻው መልከ ጼዴቅ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀዳሚ አርአያና ምሳሌ ኾኖ የታየው፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ማለትም፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ውኅደት የተገኘ በመኾኑ ነው። አማኝነታቸውንና ታማኝነታቸውን፥ ተገዢነታቸውንም፡ በአምልኮ ስግደታቸውና በቋሚ ስጦታዎቻቸው አረጋግጠው ለማሳየት ከመጡት፡ ከሦስቱ የሃይማኖት ሰዎች መካከል፡ "አንዱ፡ ኢትዮጵያዊ ነበር" ከተባለ፡ ከላይ የተገለጸውን፡ ማለትም፡ "ኢትዮጵያዊነት፡ ከሦስቱ ዘሮች ውሕደት የተገኘ፡ የመለኮታዊው ተክል ፍሬ ነው!" የሚለውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን መሠረት የሚያናጋው ይኾናል።

ስለዚህ ነው፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፥ ወደፊትም፡ የኢትዮጵያዊነታችን ሃይማኖት መሠረት እንዳይናጋ፡ ነቅተንና ተጠንቅቀን የምንጠብቀው። ይህም ማለት፡ የድኅነቱ ተስፋ፡ በአዳምና ሔዋን ተወጥኖ፡ "መልከ ጼዴቅ" በተባለው፡ በኢትዮጲስ እና "ማክዳ" በተባለችው፡ በንግሥተ ሳባ በኩልም አልፎ፡ የባለቃል ኪዳኑ፡ የዳዊት የልጅ ልጅ በኾነው፡ በቀዳማዊው ምኒልክ የትውልድ ሓረግ ተያይዞ፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ራስዋ "ኢትዮጵያ" ከተባለችው፡ ከድንግል ማርያም ደርሶ፥ ከእርሷም፡

የእግዚአብሔር ልጅ፡ ሰው ኾኖ ተወልዶና ሕማማተ መስቀልን ፈጽሞ፡ በተለይ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር የተጋቡትን፡ የተቀደሰውን ቃል ኪዳን በማፍረሳቸው፡ የጠፉትን የእስራኤልን ልጆች፥ ከዚያም፡ በክፉት ኃይል ተይዞና በጣዖት አምልኮ ታሥሮ ሲማቅቅ የኖረውን፡ የአሕዛብን ዓለም ያዳነው፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነት በመኾኑ ነው።

ይህን ኹሉ እውነታ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋገጡት መኾናቸውን፡ ባነበቧቸውና በሌሎቹ መጽሓፎቼ፥ እንዲሁም፡ በጎዋ ሰሌዳችን ላይ በወጡት መልእክቶች አማካይነት ተመልክተዋቸው ይኾናል፤ ወደፊትም፡ ሊመለከቷቸው ይቻላል። የጎዋ ሰሌዳችን አድራሻ፡ ባነበቧቸው መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል፤ እርሱም፡ www.ethkogserv.org ነው።

## ከአቶ ዮናታን የተላከ፡ ፪ኛ እ-ጦማር፤

ስለሰጡኝ በቂ ማብራሪያ፡ ከልብ አመሰግንዎታለሁ!

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች፡ አምናለሁ! ይህንም አምኜ በምፈጽመው የኢትዮጵያዊነት ምግባሬ፡ እበረታ ዘንድ፡ ገና ደካማ ነኝና፡ (በጻፍኩልዎ የክርስትና ስሜ) በጸሎትዎ አይርሱኝ!

እንዲሁም ደግሞ፡ ገና የመካነ-አእምሮ (university) ተማሪ ስለኾንሁ፡ ልጅ ነኝና፡ "አንተ!" ቢሉኝ፡ ይስማማኛል።

## ለዚህ፡ ፪ኛ እ-ጦማር የተሰጠ መልስ፡-

ለአቶ ዮናታን፡-

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትህ የጸናህ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መኾንህን፥ እንዲሁም፡ ገና የከፍተኛ ትምህርት ተከታታይ ደቀ መዝሙር መኾንህንና በጸሎት አስብህ ዘንድ፡ የክርስትና ስምህን ስለገለጽህልኝ፡ ለአንተ፡ "እግዜር ይስጥልኝ!" እላለሁ።

የዚሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ አንዱ ተጋዳይ አርበኛ ስለመኾንህ፡ እንዲህ፡ በይፋ የመሰከርከውንና ራስህን፡ ለሰማዕትነት ያዘጋጀኸውን፡ አንተን የመሰሉ ቆራጦች የኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆች መኖራችሁን፡ በየጊዜው ለሚያሳውቀኝ ፈጣሪዬና ለቅድስት እናቱ፡ ምስጋናዬን እያቀረብሁ እገኛለሁ።

በእኔ በኩል፡ በጸሎት እያዘከርሁህ ያለሁ መኾኔን ስገልጽልህ ደስ ይለኛል። በዚህ ረገድ፡ አንተም፥ እኔም፡ የበለጠ ደስ የሚያስሰኘን፡ ሌላ፡ የላቀ ምክንያት አለን፤ ይኸውም፡- እውነተኛነትህንና ታማኝነትህን፡ አንተ፡ ራስህን፡ ከምታውቀው በላይ፡ ማንነትህንና ምንነትህን ጥሩ አድርጎ የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ፡ ከዚህ የሃይማኖትህ ምስክርነት የተነሣ፡ ስምህን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፡ የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ ስለመዘገበው ነው፣ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው። (ሉቃ. ፲፥ ፲፯-፳፬)

---